# ጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ የ2023/24 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት እና

# የ2024/25 በጀት ዓመት ዕቅድ

## ጥሪያችንን አክብራችሁ የተገኛችሁ ውድ ባለአክሲዮኖች!!

ከሁሉ አስቀድሜ ለጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ 2ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንኳን በሠላም አደረሳችሁ!! እንኳን በደህና መጣችሁ እያልኩ በራሴ፣ በቦርዱ፣ በማኔጅመንቱ እና በአጠቃላይ ሠራተኞች ስም የከበረ ሠላምታየን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ፡፡

የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ሀገራችን ኢትዮጵያ የህብረተሰቡን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የፋይናንስ ተደራሽነትንና አካታችነት ለማስፋፋት የተለያዩ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች ። የፋይናንስ ሴክተሩ በኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ (NBE) የበላይ ተቆጣጣሪነት የሚመራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በስሩ፤ 32 ባንኮችን (2 የመንግስትና 30 የግል)፣ 18 የመድህን ሰጪ ኩባንያዎችን (1 የመንግስት እና 17 የግል)፣ 53 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት (9 መንግስታዊ፣ 16 መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደገፉ እና 28 የግል ማይክሮ ፋይናንሶች) ፣ 6 የመንግስት የሊዝ ኩባንያዎች እና 10 የክፍያ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የፋይናንስ አሰራሩን ይበልጥ ለማዘመን እና ተደራሽነቱን ለማስፋት በአዲስ መልክ እየተቋቋሙ ያሉ ከሀገር በቀል የፋይናንስ ተቋማት በተጨማሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በቅርቡ ባጸደቀው አዋጅ መሰረት የውጭ ባንኮች ወደ ገበያ የሚቀላቀሉበትን በር የከፈተ ሲሆን ይህም የባንኮችን ቁጥር ከፍ ከማድረጉም ባሻገር በባንኮች መካከል የተወዳዳሪነትን መንፈስ የሚያጎለብት ብሎም ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት የተቀላጠፈ፣ ምቹ እንደሚያደርግ እና አድሱ የማይክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በተሸለ መንገድ የፋየናንስ ኢንደስትሪዉን እንደሚደግፍ ይታመናል፡፡

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገኘው የቅርብ ሪፖርት እንደሚያሳየው እ.ኤ.አ ጁን 30/2024 ላይ በአጠቃላይ በሀገራችን አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት በመስት ላይ የሚገኙ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ብዛት 53 ሲሆኑ እነዚህ ተቋማት ያስመዘገቡት ካፒታል ብር 4.5 ቢሊየን ሲሆን ተጨማሪ ሌሎች አዳዲስ ተቋማት በመቋቋም ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በ53ቱ ማይክሮ ፋይናንሶች በከተማና በገጠር በድምሩ 2248 ቅርንጫፎች ተከፍተው ለህብረተሰቡ የቁጠባና ብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም ከሪፖርቱ ለመረዳት እንደተቻለው እ.ኤ.አ ጁን 30/2024 ላይ አጠቃላይ የማይክሮ ፋይናንስ የተበዳሪዎች ብዛት **9.3** ሚሊየን የደረሰ ሲሆን የመክፈያ ጊዜው ያልደረሰ የብድር መጠን ደግሞ ብር **39.7** ቢሊየን ደርሷል፡፡ ተቋማቱ ቁጠባ በማሰባሰብ ረገድም ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከላይ እስከተጠቀሰው ጊዜ ድረስ የተሰበሰበው የቁጠባ መጠን ብር **31.4** ቢሊዮን እንደደረሰ እና የደንበኞች ቁጥር 4.6 ሚሊየን እንደሆነ ከሪፖርቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ክቡራትና ክቡራን፤

### ስለ ጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማ አ.ማ ሂደት በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡-

ተቋማችን ስራ ከጀመረበት ባለፉት ሁለት ዓመታት በክልሉ ባጋጠሙ የፀጥታ ችግር ምክንያት ከፍተኛ ተግዳሮት ያጋጠመዉ ቢሆንም በቦርዱ፤ በማኔጅመንቱ እና በሠራተኞቹ ያለሰለሰ ጥረት የተቋሙ ህልዉና አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

የዚህ ሪፖርት ዓላማ እ.ኤ.አ የ2023/24 በጀት ዓመት የኩባንያውን እንቅስቃሴ ማሳየት እንደመሆኑ መጠን ከእቅድ እና ካለፈዉ አመት አፈጻጸም ጋር በማነጻጸር በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ስታንዳርድን (IFRS) መሰረት አድርጎ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማችንን የ2023/24 በጀት አመት በኦፐሬሽን እና በፋይናንስ የተከናዎኑ የሥራ እንቅስቃሴ ከእቅድ ጋር በማነጻጸር እና የቀጣይ አመት ዕቅድ እንደሚከተለዉ አቀርባለሁ፡፡

## 2. የኦፐሬሽን ስራ አፈፃፀም

### 2.1 ቁጠባን የመሰብሰብ አፈፃፀም

የተቋሙን የገንዘብ አቅም ለማጠናከር እና ለህብረተሰቡ የብድር አገልግሎት በስፋት ለማዳረስ ከብድር ደንበኞችና የብድር ደንበኛ ካልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠነ ሰፊ የሆነ ቁጠባ መሰብሰብ የግድ ነው፡፡ ስለሆነም በበጀት ዓመቱ ማኔጅመንቱና ሰራተኛው ቁጠባ በስፋት ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ በ2023/24 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ለመድረስ የታቀደው አጠቃላይ የቁጠባ መጠን 56,651,836.00 ብር ሲሆን የአመቱ አፈፃፀም 40,436,627.00 ብር መድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዓመቱ እቅድ ክንውን አፈፃፀም ሲታይ በ71% ማሳካት ተችሏል፡፡

ይህ አፈፃፀም አሁን በክልሉ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የተሻለ አፈጻጸም እንደሆነ ያሳያል፡፡

## 2.2 የብድር አፈፃፀም

ከቁጠባ አገልግሎት ቀጥሎ የፋይናንስ ተቋማት ለተጠቃሚው ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች አንዱ የብድር አገልግሎት ነው፡፡ በመሆኑም ጥራት ያለው የብድር አገልግሎት ለህብረተሰቡ በስፋት መስጠት ከብድር የሚገኘውን የተቋሙን የገቢ ምንጭ ከማሳደጉም በላይ ቁጠባ ለመሰብሰብ በር ከፋች መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም የብድር አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም በብድር ስርጭት፣ በብድር አሰባሰብ፣ እና በተበዳሪዎች እጅ ላይ የሚኖረውን የብድር መጠን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ የተሻለ ስራ ተሰርቷል፡፡

በዚሁ መሰረት የበጀት ዓመቱ የብድር ስራ እቅድ አፈፃፀምና የተገኘው ውጤት ካለፈው ተመሳሳይ የበጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ነው፡፡

በጀት ዓመቱ ጠቅላላ ሊሰራጭ የታቀደው የብድር መጠን 160,000,000.00 ብር ሲሆን የተሰራጨው የብድር መጠን ብር 71,252,856.00 ነው፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 44% ሲሆን ካለፈው ተመሳሳይ 98,986,100.00 ጋር ሲነፃፀር የብር የ27,733,244.00 ብር ቅናሽ ያሳያል፡፡ በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ሊሰበሰብ የታቀደው የብድር መጠን 52,663,885 ብር ሲሆን የተሰበሰበው የብድር መጠን ብር 47,827,144.00 ነው፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 90% ነው፡፡ በ2023/24 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በተበዳሪዎች እጅ ይኖራል ተብሎ የታቀደው የብድር መጠን 188,776,998 ብር ሲሆን ክንውኑ 105,486,813 ብር ነው፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 55% ሲሆን ባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው የብድር መጠን ከብር 81,440,883 ጋር ሲነፃፀር የብር 24,045,930 ብልጫ አለው፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ከ90 ቀን በላይ ሳይከፈል የቆየ ውዝፍ ውስጥ የገባ ብድር መጠን ብር 1,146,794 ሲሆን የተቋሙ ውዝፍ ውስጥ የገባ ብድር ምጣኔ 1.10 በመቶ ነው፡፡ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 5% ዝቅተኛ መመዘኛ የተሻለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ እንዲሆን ብድር በማስመለስ .ሂደት ውስጥ ሠራተኛው ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን ይህ ውጤት አንዱ ማሳያ ነው፡፡

## 2.3 አዲስ ቅርንጫፎችን መክፈት

ቅርንጫፎች ተቋሙንና የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቀሚዎችን አገናኝ ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት በየጊዜው የአዋጪነት ጥናት እየተደረገ የቅርንጫፎችን ቁጥር መጨመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በክልሉ ባጋጠመዉ ጸጥታ ችግር እና የገንዘብ እጥረት ምክንያት ከሁለት ቅርንጫፎች በላይ መክፈት አልተቻልም፡፡ በዚህም መሰረት ተቋሙ አሁን ያሉት ቅርጫፎች ብዛት ሰባት ብቻ ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ አዲስ አበባ ከተማ አዲሱ ገበያ ቅርንጫፍ የተከፈው ነው፡፡

# 3. የፋይናንስ ሥራ አፈፃፀም

## 3.1 ሀብት

ኩባንያው አጠቃላይ ያለው የሀብት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ በ2023/24 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የተቋሙ የሀብት መጠን ብር 131,207,796 ነው፡፡ ይህም ባለፈው አመት ከነበረው በጠቅላላ 106,414,453 ሲነፃፀር በብር 24,793,343 ብልጫ አለው፡፡ ይህም የተቋሙ እድገት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ተቋሙ አጠቃላይ ካለው ሀብት ውስጥ የ80 በመቶ ድርሻውን የሚይዘው ከብድር የሚሰበሰብ ሀብት በመሆኑ ገቢ ሊያስገኝ የሚችል የሀብት መጠን አሁንም ከፍተኛውን ድርሻን ይዟል፡፡ በመሆኑም ይህ የተቋሙን ጤናማ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 3.2 እዳ

ተቋሙ የኦፐሬሽን ስራን ለማስፋፋት ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ ቁጠባ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በጠቅላላ በዓመቱ 40,436,627 ቁጠባ መሠብሰብ ችሏል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ ባንኮች ብድር ለማግኘት የተሞከረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ብድር ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህም በብድር ስርጭት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊፈጥር ችሏል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በያዝነው በጀት ዓመት ተቋሙ ከባንኮች የተሻለ ብድር ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 3.3 ካፒታል

ባለፈዉ ዓመት በተካሄደዉ 1ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተቋሙን ከፒታል ወደ ብር 500 ሚሊየን ለማድረስ በተወሰነዉ መሰረት ቃለ ጉባኤዉን በብሔራዉ ባንክ በማጸደቅ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ለነባር 1107 እና ለአዲስ ባለ አክሲዮኖች 772 አክስዮኖች በድምሩ 1,879 የአክሲዮን መጠን በብር 9,395,000 ለመሸጥ ተችሏል፡፡ አሁን የተቋሙ ከፒታል ወደ 87,385,119 ከፍ ብሏል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ባለአክሲዮኖች አክሲዮን በመግዛት ካፒታላችሁን እንድታሳድጉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪዉን ያቀርባል፡፡

## 3.4 ገቢ

ጣና ማይክሮ ፋይናንስ የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የአክሲዮን ማህበሩ ዋነኛው የገቢ ምንጭ ከብድር የሚሰበሰብ ወለድ ሲሆን ተጨማሪ የገቢ ምንጮች የአገልግሎት ክፍያ፣ የብድር ኢንሹራንስ፣ ከቁጠባ የሚገኝ ወለድና ሌሎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በያዝነው የበጀት አመት የተሰበሰበው ጠቅላላ የገቢ መጠን ብር 23,827,811.19 ሲሆን ይህም በበጀት ዓመት ውስጥ ለመሰብሰብ ከታቀደው የገቢ መጠን ከብር 39,985,039 ጋር ሲነፃፀር ክንውኑ 59% ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ተቋሙ በአመቱ ዉስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥም ሆኖ የተሻለ ተግባር ያከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 3.5 ወጪ

በ2023/24 በጀት ዓመት ለሠራተኞች ደመወዝ፣ ለቢሮ ኪራይ፣ ለቁጠባ ወለድ፣ ለኮር ባንክንግ አገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ለሌሎች አስተዳደራዊ እና ለኦፕሬሽን ተግባራት የብር 25,237,389 ወጪ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን እስከ በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተመዘገበው አጠቃላይ የወጪ መጠን 17,978,977 ብር ነው፡፡ ይህም ከታቀደው ወጪ 71% ያህል ወጪ እንደተመዘገበ የሂሳብ መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከተመዘገቡት ወጪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻውን የሚይዙት የሰራተኛ ደመወዝ ወጪ፣ የቁጠባ ወለድ ወጪ፣ የቢሮ ኪራይ ወጪ እና ቋሚ ዕቃዎች እርጅና ቅናሽ ወጪዎች ናቸው፡፡

## 3.6 ትርፍ

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 14,088,969 ብር ለማትርፍ የታቀደ ሲሆን ማትረፍ የተቻለው 5,851,402 ብር ነው፡፡ ይህም የበጀት ዓመቱ እቅድ ክንውን አፈፃፀም ሲታይ ማሳካት የተቻለው 41% ሲሆን አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲታይ እጅግ አመርቂ አፈፃፀም ነው ብለን እናምናለን፡፡

## 3.7 የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጨማሪ የሥራ እንቅስቃሴ

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ መደበኛ፣ አስቸኳይ እና የንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በማካሄድ ቀጥሎ የተመለከቱትን አበይት ተግባራት አከናውኗል፡፡

- የተቋሙን የሥራ አፈፃፀም በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ እና በዓመት መጨረሻ በመገምገም አስፈላጊ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡
- የተቋሙን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት መርምሮ አፅድቋል፡፡
- ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን እንዲላክ አጽድቋል፡፡

- የተቋሙን መዋቅራዊ ጥናት አስጠንቶ አጽድቋል፡፡
- ከተቋሙ እድገት ጋር የተመጣጠነ አመራር ለመስጠት እና ሥራዎችን ለመከታተል እንዲያመች ሁለት ንዑሳን ኮሚቴዎች በማቋቋም የተለያዩ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡
- የብድር ወለድ ምጣኔ እና የቁጠባ ወለድ ምጣኔ ማሻሻያዎችን አጽድቋል፡፡
- የተቋሙን ድህረ ገጽ (ዌብ ሳይት) በባለሙያ እንዲለማ በማድረግ ስራ ላይ እንዲዉል አድርጓል፡፡ (www.tanamfi.com)
- ተቋሙ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት የተሻለ እንዲሆን ከተቋሙ ማኔጅመንት ጋር አብሮ እቅዶችን በማውጣት አከናውኗል፡፡

## 4. በሥራ ላይ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 4.1 ያጋጠሙ ችግሮች

**በበጀት ዓመቱ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ችግሮች አጋጥመዋል፡-**

- በክልሉ ያጋጠመው የፀጥታ ችግር የንግድ እንቅስቃሴው እንዲቀዘቅዝ በማድረጉ ምክንያት በቁጠባ እና ብድር እንቅስቃሴው ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡
- በክልሉ በተፈጠረው የኢንተርኔት መቆራረጥ ምክንያት ከተለያዩ ተቋማት ጋር የምናደርገውን የመረጃ ልውውጥ አስቸካሪ ማድረጉ በስራ ሂደት ላይ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡
- በሃገሪቱ ባጋጠመው የገንዘብ ግሽበት ምክንያት ለብድር እና ለተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚውል ገንዘብ እጥረት መከሰቱ ስራችን አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡
- በባንኮች ላይ የብድር ገደብ በብሔራዊ ባንክ በመጣሉ ምክንያት ከባንኮች ብድር ለማግኘት የተደረገዉ ጥራት ሊሳካ አለመቻሉ፡፡

### 4.2 ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- በክልሉ ባጋጠመው የፀጥታ ችግር ምክንያት ያጋጠመውን የብድር ገንዘብ እጥረት ለመቅረፍ ከክልሉ ውጪ አዲስ አበባ ከተማ ላይ አንድ ቅርንጫፍ በመክፈት ስራ ለመስራት ተሞክሯል፡፡
- በክልሉ ያጋጠመውን የመረጃ እጥረት ለመቅረፍ ተቋሙ የጀመረውን የኮር ባንኪንግ ስራ በዚህ በጀት ዓመት ተግባራዊ በማድረግና በማጠናቀቅ በተቋሙ አሰራር ላይ ጉልህ ውጤት ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- የብድር ገንዘብ እጥረትን ለመቅረፍ እና ቁጠባን ለማበረታታት ከፍተኛ የቁጠባ ወለድ በመስጠት እና የተለያዩ የቁጠባ አማራጮችን ለህብረተሰቡ በመስጠት ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል፡፡ የተቋሙ

ባለአክሲዮኖች በዚህ በተመቻቸው የቁጠባ አማራጭ ተጠቃሚ በመሆን እና ሌሎችንም በመጋበዝ ከጎናችን እንድትሆኑ የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ቦርድ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 5. የ2024/2025 በጀት ዓመት የሥራ እቅድ በጨረፍታ

- ለ1515 ተበዳሪዎች ብር 256 ሚሊዮን ብር በማሰራጨት አመታዊ ገቢን ወደ ብር 53 ሚሊዮን በማሳደግ እና ብር 15 ሚሊዮን ትርፍ ለማስገኘት እቅድ ተይዟል፡፡ ለተለያዩ ለካፒታልና መደበኛ ወጪዎች ብር 38 ሚሊዮን ወጪ ይወጣል ተብሎ ታቅዷል፡፡
- የ2024/2025 በጀት ዓመት አጠቃላይ የብድር ተመላሽ /Loan Repayment/ ወደ ብር 84 ሚሊዮን ለማድረስ እቅድ ተይዟል፡፡
- የ2024/2025 በጀት ዓመት የመሰብሰቢያ ጊዜ ያልደረሰ የብድር ደንበኞች ቁጥር 2276 ለማድረስ እና የብድሩን መጠን 272 ሚሊዮን ለማድረስ እቅድ ተይዟል፡፡
- በበጀት ዓመቱ 4 አዲስ ቅርንጫፎችን በመክፈት የቅርንጫፎችን ቁጥር 11 ለማድረስ እቅድ ተይዟል፡፡
- በ2024/2025 በጀት ዓመት ተቋሙን በከፍተኛ ደረጃ በማስተዋወቅ የተሸለ አክሲዮን ለመሸጥ፣ ከፍ ያለ ቁጠባ ለመሰብሰብ እና ከባንኮች ብድር ለማግኘት እቅድ ተይዟል፡፡
- በበጀት ዓመቱ የተቋሙን ኮር ባንኪንግ ሲስተም አጠናቆ ወደ ትግበራ ለመግባት እቅድ ተይዟል፡፡
- አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማስፋት የተሻለ ቁጠባና የብድር አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ ተይዟል፡፡

በመጨረሻም እነዚህን እቅዶች ከግብ ለማድረስ ከባለሃብቱ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያስፈልገን በመሆኑ ይህንኑ አውቃችሁ ከወዲሁ ከፍተኛ እገዛ እንድታደርጉልን በራሴና በቦርዱ ስም ጥሪየን እያቀረብኩ በዚሁ አጋጣሚ የተቋሙን የሥራ አመራር ቦርድ፣ ማኔጅመንቱን እና ሠራተኞቹን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ላሳዩት ትጋት ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

## ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡